# Overview of Early Intervention Dispute Resolution Processes for Families of Infants & Toddlers (Birth to Age 3) (ለጨቅላ ህጻናት እና ታዳጊዎች ቤተሰቦች (ከልደት እስከ 3 አመት) የቅድመ ጣልቃ ገብነት ግጭት አፈታት ሂደቶች አጠቃላይ ዕይታ)

** በልዩ ትምህርት አግባብ ላለው ግጭት አፈታት ማዕከል ለWashington ግዛት የተስተካከለ*



CADRE (2018)። የCADRE ፈጣን መመሪያ ለቅድመ ጣልቃ ገብነት የግጭት አፈታት ሂደቶች ለጨቅላ ህጻናት እና ታዳጊዎች ወላጆች (ከልደት እስከ 2)፣ Eugene፣ Oregon፣ CADRE። የታተመበት ቀን፡- መስከረም 2018።

| Processes (ሂደቶች) | Mediation (ሽምግልና) | Administrative Complaint (የአስተዳደር ቅሬታ) | Due Process Hearing (የፍትህ ሂደት ችሎት) |
|---|---|---|---|
| ሂደቶቹ እንዴት እንደሚለያዩ | ሰዎችን ከገለልተኛ፣ ብቁ እና የሰለጠነ አስታራቂ ጋር የሚያገናኝ፣ እርስ በርሳቸው እንዲግባቡ፣ ስጋታቸውን እንዲገልጹ እና አለመግባባቶችን እንዲፈቱ የሚረዳ በፈቃደኝነት የሚደረግ ሂደት። | አገልግሎት አቅራቢ፣ አቅራቢ ኤጀንሲ፣ የግዛት መሪ ኤጀንሲ ወይም ሌላ የህዝብ ኤጀንሲ የ IDEAን ክፍል C እንዳልተከተሉ እና በግዛቱ ውሳኔ እንዲሰጥ ለመጠየቅ በጽሑፍ የቀረበ ጥያቄ። | በወላጅ የቀረበ ቅሬታ ለመፍታት የሚያገለግል ሂደት። |
| ምን ጉዳዮች እና መቼ ጥቅም ላይ እንደሚውሉ | በማንኛውም ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውለው በIDEA ክፍል C ውስጥ ካለው አገልግሎት አቅርቦት ጋር በተያያዘ በወላጆች እና በአቅራቢ ኤጀንሲ ወይም በአገልግሎት አቅራቢ መካከል አለመግባባት በሚፈጠርበት ጊዜ ነው። በማንኛውም ጊዜ ሊጠየቅ ይችላል፣ የፍትህ ሂደት ችሎት ጥያቄ ከቀረበ በፊት ወይም ሲቀርብ፣ ወይም የአስተዳደር ቅሬታ ሲቀርብ ጨምሮ። | የአንድ የተወሰነ ጨቅላ/ሕጻን እና ቤተሰቦቻቸውን ወይም የግዛት አቀፋዊ የሥርዓት ጉዳዮችን በተመለከተ የIDEA ክፍል C ደንቦች ተከትለዋል ወይ የሚል ጥያቄ በሚኖርበት ጊዜ ጥቅም ላይ ይውላል። | የሕፃን ወይም የጨቅላ መታወቂያ፣ ግምገማ ወይም ምደባ፣ ወይም ለጨቅላ ሕፃን ወይም ታዳጊ ሕፃን እና የልጁ ቤተሰብ የቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶችን በተመለከተ አለመግባባቶችን ለመፍታት ይጠቀማል። |
| ማን ይጀምራል/ያነሳሳል | አንድ የቤተሰብ አባል፣ አገልግሎት አቅራቢ፣ አቅራቢ ኤጀንሲ እና/ወይም የህዝብ ኤጀንሲ ሽምግልናን ሊጠይቅ ይችላል። ተሳትፎ ለሁሉም ወገኖች በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ነው። | ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት፣ ሌላው ቀርቶ ከሌላ ግዛት እንኳን የመጣ፣ የአስተዳደር ቅሬታ ማቅረብ ይችላል። | የፍትህ ሂደት ችሎት ጥያቄ ማቅረብ የሚችሉት ወላጅ ብቻ ናቸው። |
| ውጽዓት ወይም ተፈላጊው ውጤት | የተፈረመ፣ በሕጋዊ መንገድ የሚተገበር፣ የጽሑፍ ስምምነት። | ግኝቶችን እና መደምደሚያዎችን ያካተተ እና ለመጨረሻው ውሳኔ ምክንያቶችን የሚዘረዝር የጽሑፍ ውሳኔ። የIDEA ክፍል C አልተከተለም የሚል ግኝት ካለ፣ ሪፖርቱ ከቅሬታው ጋር በተገናኘ የጨቅላ/ሕፃን እና ቤተሰብ ፍላጎቶችን ለማሟላት የሚያስፈልጉ የእርማት እርምጃዎችን ማካተት አለበት። | የተፃፉ የእውነታ ግኝቶች እና ውሳኔዎች። ውሳኔው የተወሰኑ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ሊያዝ ይችላል። |

| Processes (ሂደቶች) | Mediation (ሽምግልና) | Administrative Complaint (የአስተዳደር ቅሬታ) | Due Process Hearing (የፍትህ ሂደት ችሎት) |
|---|---|---|---|
| የሂደቱ ልዩነቶች | የሽምግልና ውይይቶች ሚስጥራዊ ናቸው እና በፍትህ ሂደት ችሎት ወይም በፍትሐ ብሔር ክስ ተቀባይነት የላቸውም።<br><br>ሽምግልና ተለዋዋጭ ሂደት ነው - ተሳታፊዎች በሂደቱ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳርፉ እና በመጨረሻም ውጤቱን ሊወስኑ ይችላሉ።<br><br>አስታራቂው ውሳኔ አይሰጥም። ሁሉም ተሳታፊዎች በሽምግልና ስምምነት ውስጥ በማንኛውም ውሳኔ መስማማት አለባቸው። | ከልጁ ጋር ግንኙነት የሌላቸውን ጨምሮ ለማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት ክፍት የሆነው ብቸኛው የግጭት መፍቻ አማራጭ ይህ ነው።<br><br>የመጨረሻው ውሳኔ ሕጻን-ተኮር የሆኑ ወይም ከሥርዓተ-አቀፍ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ የእርማት እርምጃዎችን ሊያካትት ይችላል።<br><br>ቅሬታ አቅራቢው ስለ ስጋቶቹ ተጨማሪ መረጃ ለመስጠት እድሉ ይኖረዋል። ይህ መረጃ በቃልም ሆነ በጽሑፍ ሊቀርብ ይችላል። | ወላጆቹ ያለምንም ክፍያ የችሎቱን የጽሑፍ ወይም የኤሌክትሮኒክስ የቃል ግልባጭ የማግኘት መብት አላቸው።<br><br>የችሎቱ ሃላፊው ውሳኔ በክልል ወይም በፌዴራል ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊባል ይችላል። |
| ጥቅማ ጥቅሞች | ውይይቶች ሚስጥራዊ ናቸው - በሽምግልና ውስጥ የተነገረው በፍትህ ሂደት ችሎት ወይም በፍትሐ ብሔር ክስ እንደ ማስረጃ ሊያገለግል አይችልም።<br><br>ሽምግልና በጽሑፍ ከመንግስት ቅሬታዎች ወይም የፍትህ ሂደት ችሎቶች የበለጠ ተለዋዋጭ፣ አነስ ያለ ተቃራኒ/አነጋጋሪ አማራጭ ያቀርባል።<br><br>አንዳንድ ጊዜ ተሳታፊዎች ሂደቱን ለመንደፍ ከአስታራቂው ጋር ይሠራሉ። በአንዳንድ ሁኔታዎች ተሳታፊዎች አስታራቂውን አንድ ላይ እንዲመርጡ ሊፈቀድላቸው ይችላል።<br><br>ሽምግልና ከጽሑፍ የስቴት ቅሬታዎች ወይም የፍትህ ሂደት ችሎቶች በበለጠ ፍጥነት አለመግባባቶችን ለመፍታት ይረዳል። | በልዩ ሁኔታዎች ምክንያት የጊዜ ሰሌዳው ካልተራዘመ በስተቀር ቅሬታው ከደረሰ ከ 60 **የቀን መቁጠሪያ** ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የጽሑፍ ውሳኔ መሰጠት አለበት።<br><br>አስተዳደራዊ ቅሬታ ለማቅረብ በአንፃራዊነት ቀላል ነው። | ገለልተኛ ሦስተኛ ወገን ተዋዋይ ወገኖች በራሳቸው ሊፈቱ የማይችሉትን ጉዳዮች እንዲወስኑ እድል ይሰጣል።<br><br>የፍትህ ሂደት ቅሬታ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ውሳኔው የመጨረሻ እስከሚሆን ድረስ፣ አቅራቢ/መሪ ኤጀንሲ እና ወላጆች ካልተስማሙ በስተቀር፣ ልጁ በወላጆች ስምምነት እውቅና ያገኘው IFSP ውስጥ በተገለፀው ሁኔታ ተገቢውን የቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎት ማግኘቱን መቀጠል ይኖርበታል።<br><br>የፍትህ ሂደት ቅሬታ በክፍል C ውስጥ ለመጀመሪያ አገልግሎቶች ማመልከቻን የሚያካትት ከሆነ ህፃኑ በግጭት ውስጥ የማይገኙ አገልግሎቶችን ማግኘት አለበት።<br><br>ይግባኝ ካልተባለ በቀር፣ የችሎቱ ሃላፊ ውሳኔ በአገልግሎት አቅራቢው/በግዛት መሪ ኤጀንሲ እና በወላጆች ላይ በሕጋዊ መንገድ የሚሠራ/የሚከናወን ነው። |



| Processes<br>(ሂደቶች) | Mediation<br>(ሽምግልና) | Written State Complaint<br>(የተጻፈ የግዛት ቅሬታ) | Due Process Hearing Request<br>(የፍትህ ሂደት ችሎት ጥያቄ) |
|---|---|---|---|
| ግምት ውስጥ የሚገቡ | ሽምግልና በፈቃደኝነት ነው፣ ስለዚህ የቤተሰብ አባል፣ የEIS አቅራቢ፣ አመራር ኤጀንሲ እና/ወይም የህዝብ ኤጀንሲ ለመሳተፍ መስማማት አለባቸው።<br>የችግሮቹ መፍትሄ መኖሩ ወይም ስምምነት መፈጠሩ በተሳታፊዎች ላይ የተመሠረተ ነው።<br>ውስብስብ ሁኔታዎች ስምምነት ላይ ለመድረስ ብዙ የሽምግልና ክፍለ ጊዜዎችን ሊፈልጉ ይችላሉ።<br>የጽሑፍ ስምምነት ለመፈጠሩ ምንም ዋስትና የለም። | ቅሬታውን የሚያቀርበው ሰው ወይም ድርጅት IDEA አልተከተለም የሚለውን ስጋት የሚደግፉ እውነታዎችን ማቅረብ አለበት። የግዛት ቅሬታ በጽሑፍ መፈረም አለበት። **ማስታወሻ**፦ በግል የሚለይ መረጃን ለሦስተኛ ወገን ለመልቀቅ የወላጅ ፈቃድ ያስፈልጋል።<br>ይህ ሂደት ተሳታፊ የሆኑትን አለመግባባቶችን በትብብር ለመፍታት እንዲሞክሩ አይፈልግም። ሆኖም፣ ሽምግልና በማንኛውም ጊዜ እንደተገኘ ሆኖ ይቆያል።<br>IDEA ግዛቶች ለጽሑፍ ውሳኔ የይግባኝ ሂደት እንዲያቀርቡ አይጠይቅም። ይግባኝ ከተፈቀደ፣ ለመጨረሻ ውሳኔ የ60 የቀን መቁጠሪያው የጊዜ ሰሌዳ አሁንም ተፈጻሚ ነው። ሊኖሩ ስለሚችሉ አማራጮች ከግዛትዎ መሪ ኤጀንሲ ጋር ያረጋግጡ። | ውሳኔው በችሎቱ ሃላፊ የሚሰጥ ሲሆን እነሱም የሚከተሉትን መሆን አለባቸው፦<br>• በቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች አቅርቦት ወይም ልጅን በመንከባከብ የመሪ ኤጀንሲ ተቀጣሪ ወይም የቅድሚያ ጣልቃ ገብነት አገልግሎት አቅራቢ አይደሉም፤<br>• ሂደቱን ለመተግበር ከዓላማው ጋር የሚጋጭ የግል ወይም የሙያ ፍላጎት የላቸውም።<br>የችሎት ሃላፊ ውሳኔ ይግባኝ ከተባለ፣ ይግባኙ እስኪጠናቀቅ ድረስ ውሳኔው ተግባራዊ ሊሆን አይችልም።<br>መሪ ኤጀንሲው በጠበቃ ሊወከል ይችላል። ወላጁ ጠበቃ ቢቀጥር በወላጁ ወጪ ነው። |
| ውሳኔ ሰጪ | የጨቅላ/ሕጻናት ወላጆችን ጨምሮ ተሳታፊዎች በጋራ መፍትሄዎች ላይ ይሠራሉ እና ውጤቱ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራሉ። | ቅሬታው መፈታቱን የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለበት ግዛቱ ነው፣ እና ስለ ቅሬታው ገለልተኛ ውሳኔ ይሰጣል። | የሕፃን ወይም የጨቅላ መታወቂያ፣ ግምገማ ወይም ምደባ፣ ወይም ለጨቅላ ሕፃን ወይም ታዳጊ ሕፃን እና የልጁ ቤተሰብ የቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶችን በተመለከተ አለመግባባቶችን ለመፍታት ይጠቀማል። |
| የሦስተኛ ወገኑ ሚና | **ሽማግሌ** በተለምዶ፦<br>• ተሳታፊዎች ለክፍለ-ጊዜው መሰረታዊ ሕጎችን እንዲያዘጋጁ ይረዳል።<br>• ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢ ይፈጥራል እና ተሳታፊዎች የሌሎችን አመለካከት እንዲያከብሩ ያበረታታል።<br>• ውይይትን በማዳመጥ፣ ፍላጎቶችን በመለየት እና ስጋቶችን በማብራራት ይመራል።<br>• ውሳኔ አይሰጥም።<br>• ከልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች ጋር በተያያዙ ሕጎች ላይ እውቀት አለው። | **ቅሬታ መርማሪ**፦<br>• ከቅሬታ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን ይመረምራል።<br>• ከቅሬታ ጋር ከተያያዙ ሰዎች ጋር ቃለ መጠይቅ ማድረግ ወይም መገናኘት ይችላል።<br>• በሚመለከተው ህግ ላይ በመመስረት ግኝቶችን እና ውሳኔዎችን ያደርጋል። | **የችሎቱ ሃላፊ**፦<br>• ሁሉንም የቅድመ ችሎት እንቅስቃሴዎችን ጨምሮ የችሎት ሂደቱን ይቆጣጠራል።<br>• ችሎቱን ያካሂዳል እና የአሰራር ጉዳዮችን ይቆጣጠራል።<br>• በምስክርነት እና በችሎቱ ላይ በቀረቡት ሌሎች ማስረጃዎች ላይ በመመስረት ውሳኔን ለመጻፍ የሚመለከተውን ሕግ ይጠቀማል።<br>• ከችሎቱ በፊት ጉዳዮቹ ከተፈቱ የፍትህ ሂደት ቅሬታውን (የችሎቱን ጥያቄ) ውድቅ ሊያደርግ ይችላል። |
| የጊዜ ገደብ | ምንም የጊዜ መስመር አልተገለጸም። በጊዜ መርሐግብር የተያዘለት እንዲሆን ይጠይቃል።<br>• ሽምግልና የቤተሰብን የፍትህ ሂደት የማግኘት መብት ለመከልከል ወይም ለማዘግየት ወይም በ IDEA ክፍል C ስር ያሉ ሌሎች መብቶችን ለመከልከል ጥቅም ላይ ሊውል አይችልም። | በIDEA ስር፣ ግለሰቡ ችግሩን ካወቀ ወይም ማወቅ ከነበረበት ቀን ጀምሮ በአንድ አመት ውስጥ የግዛት ቅሬታዎች በጽሑፍ መቅረብ አለባቸው።<br>• ልዩ በሆኑ ሁኔታዎች የጊዜ ሰሌዳው ካልተራዘመ ወይም ተዋዋይ ወገኖች በሽምግልና ሂደት ውስጥ ለመሳተፍ ጊዜውን ለማራዘም ካልተስማሙ በስተቀር ቅሬታው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ የጽሑፍ ውሳኔው ከ60 **የቀን መቁጠሪያ** ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መሰጠት አለበት። | IDEA የማመልከቻ ጊዜ ገደብን አይገልጽም። በልጅዎ አገልግሎቶች ላይ ያለዎት ስጋት በአፋጣኝ መፍትሄ መሰጠቱን ለማረጋገጥ በጊዜው ማስገባት አስፈላጊ ነው።<br>• የፍትህ ሂደቱ ቅሬታ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ በ30 **የቀን መቁጠሪያ** ቀናት ውስጥ ችሎቱ መጠናቀቅ እና የችሎቱ ውሳኔ መስጠት አለበት። |

| Processes (ሂደቶች) | Mediation (ሽምግልና) | Written State Complaint (የተጻፈ የግዛት ቅሬታ) | Due Process Hearing Request (የፍትህ ሂደት ችሎት ጥያቄ) |
|---|---|---|---|
| የፋይናንስ ወጪዎች / ማን ይከፍላል | ለቤተሰቡ ምንም ወጪ የለም። አስታራቂዎች/ሽማግሌዎች እና መገልገያዎች በመንግስት ወጪ ነው የሚቀርቡት። | ለቤተሰቡ ምንም ወጪ የለም። ምርመራው የሚካሄድው እና ውሳኔው የሚሰጠው በመንግስት ወጪ ነው። | ችሎቱ፣ የችሎት ሃላፊው፣ መገልገያዎቹ እና ውሳኔው ለወላጆች ምንም ዋጋ የሌላቸው መሆን አለባቸው።<br><br>እያንዳንዱ አካል የራሱን ወጪዎች ይሸፍናል፣ ይህም የጠበቃ ክፍያዎችን እና የምስክር ክፍያዎችን ያካትታል። |
| በግንኙነቶች ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ | ሽማግሌው ተሳታፊዎችን ችግሩን በብቃት እንዲፈቱ ሊረዳቸው ይችላል።<br><br>የተሻለ ንግግር እና የተሻሻሉ ግንኙነቶች ብዙውን ጊዜ ከሽምግልናዎች የሚመነጩ ውጤቶች ናቸው። | ይህ ሂደት በግንኙነቶች ላይ አያተኩርም። | የፍትህ ሂደት ሁሉንም ያማከለ የግጭት አፈታት ሂደት ተደርጎ ይወሰዳል። |
| እንዴት መዘጋጀት እንደሚቻል<br><br>ተጨማሪ ግባዓቶች በCADRE ድህረ ገጽ ላይ ይገኛሉ<br><br>**www.cadreworks.org** | የሚከተሉትን ማድረግ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል፡-<br><br>• ለመወያየት የሚፈልጓቸውን ጉዳዮች እና መጠየቅ የሚፈልጓቸውን ጥያቄዎች ዝርዝር ያዘጋጁ።<br>• ለልጅዎ እና ለቤተሰብዎ ፍላጎቶች በጣም አስፈላጊ የሆነውን ያስቡ።<br>• ለማዳመጥ ፈቃደኛ ይሁኑ እና የሌሎችን ሃሳቦች እና እንዲሁም መፍትሄዎችን በጥንቃቄ ግምት ውስጥ ያስገቡ።<br>• ሰነዶችን ያደራጁ፣ ቀናትን እና ማስታወሻዎችን በላያቸው ላይ ያስቀምጡ እና ለማጋራት ተጨማሪ ቅጂዎችን ይዘው ይምጡ።<br>• ሌሎችን ለማስረዳት ወይም ለማሳወቅ የሚረዱ ቁሳቁሶች/ሰነዶችን ይዘው ይምጡ።<br>• በስብሰባው ወቅት ስሜቶችን እንዴት እንደሚቋቋሙ ያስቡ።<br>• ለመሳተፍ ለመዘጋጀት የበለጠ ጊዜ እንዲኖርዎት ከስብሰባው ትንሽ ቀደም ብሎ ይድረሱ። | ቅሬታውን የሚያቀርበው ሰው የሚከተሉትን ማቅረብ አለበት፡-<br><br>• አቤቱታው/ቅሬታው በሚቀርብበት ጊዜ IDEA አልተከተለም የሚለውን ጥያቄ ለመደገፍ የሚያስፈልጉትን መረጃዎች በሙሉ ያካትቱ።<br>• በተመሳሳይ ጊዜ ቅሬታው ለግዛቱ ሲቀርብ፣ ቅሬታ አቅራቢው የቅሬታውን ግልባጭ ለ EIS አቅራቢ፣ ለክልሉ መሪ ኤጀንሲ ወይም ቅሬታው ለሚቃወም አካል ማቅረብ አለበት።<br>• ስለ ቅሬታው ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ሁሉንም ጥያቄዎች በጊዜው ምላሽ ይስጡ።<br><br>ሁሉንም የልጁን መዝገቦች እና ሌሎች ሰነዶች ማደራጀት እና ይህ መረጃ ኤጀንሲው መስፈርቶቹን ያልተከተለ መሆኑን ለማሳየት ዝግጁ መሆን ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። | ጉዳዩን በበቂ ሁኔታ ለማቅረብ በደንብ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል።<br><br>ወገኖች ለችሎት የሚከተሉትን ለማድረግ ዝግጁ መሆን አለባቸው፡-<br><br>• መረጃን መሰብሰብ እና ማቅረብ<br>• የምስክርነት፣ የምስክሮች ዝርዝር እና ሌሎች የችሎት ሰነዶችን ያዘጋጁ<br>• ምስክሮችን መጠየቅ እና ድጋሚ መመርመር<br><br>ወገኖች ጠበቃ ለመቅጠር ወይም ላለማማከር ይመርጣሉ። በጠበቃ ያልተወከለ ሰው “pro se (ፕሮሴ)” ተብሎ ሊጠራ ይችላል። ይህ የላቲን ቃል ሲሆን እሱም ሰውዬው እራሱን ወይም እራሷን በህግ ሂደት ውስጥ ሉወክላሉ ማለት ነው። |

CADRE ይህንን ሰነድ ያዘጋጀው በU.S. Department of Education (አሜሪካ የትምህርት ክፍል) የOffice of Special Education Programs (ልዩ ትምህርት ፕሮግራሞች ቢሮ) በትብብር ስምምነት ቁጥር H326X130001 ነው። Tina Diamond, Ph.D.፣ የፕሮጀክት ኦፊሰር ሆና አገልግላለች። እዚህ የተገለጹት አመለካከቶች የግድ የU.S. Department of Education (አሜሪካ የትምህርት ክፍል) ቦታዎችን ወይም ፖሊሲዎችን አይወክሉም። በዚህ እትም ውስጥ የተጠቀሰው ማንኛውም ምርት፣ ሸቀጥ፣ አገልግሎት ወይም ኢንተርፕራይዝ በU.S. Department of Education (አሜሪካ የትምህርት ክፍል) ምንም አይነት ይፋዊ ድጋፍ የታሰበ ወይም ሊታሰብበት አይገባም። ይህ ምርት የህዝብ ንብረት ነው። ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ለማባዛት ፍቃድ ተሰጥቷል። ይህን ሕትመት እንደገና ለማተም ፈቃድ አስፈላጊ ባይሆንም፣ ጥቅሱ፡- CADRE (2018) መሆን አለበት። የCADRE *ፈጣን መመሪያ ለቅድመ ጣልቃ ገብነት የግጭት አፈታት ሂደቶች ለጨቅላ ህጻናት እና ታዳጊዎች ወላጆች (ከልደት እስከ 2)*፣ Eugene፣ Oregon፣ CADRE። የታተመበት ቀን፡- መስከረም 2018።

**ይህ አጠቃላይ ዕይታ ማንኛውንም IDEA ክፍል C የሥርዓት መከላከያዎችን ወይም የፌዴራል ወይም የክልል ህግ መስፈርቶችን ለመተርጎም፣ ለማሻሻል ወይም ለመተካት የታሰበ አይደለም።**

በልዩ ትምህርት ተገቢ የግጭት አፈታት ማዕከል፡-

**(541) 359-4210** **cadre@directionservice.org** **www.cadreworks.org**

---

*DCYF ኢያዳላም እንዲሁም ፕሮግራሞቹን እና አገልግሎቶቹን ለሁሉም ሰው ዘር፣ ቀለም፣ ጾታ፣ ሃይማኖት፣ እምነት፣ የትዳር ሁኔታ፣ ብሄራዊ ማንነት፣ የዜግነት ወይም የስደተኝነት ሁኔታ፣ ዕድሜ፣ ጾታዊ ዝንባሌ ወይም የፆታ ማንነት፣ የአርበኛ ወይም የውትድርና ሁኔታ፣ የምታጠባ እናት ሁኔታ እንዲሁም ምንም አይነት የአካል፣ የስሜት ህዋሳት ወይም የአዕምሮ ስንኩልነት መኖር ወይም ውሻ የመመሪያ ወይም አገልግሎት ሰጪ እንስሳትን ቢጠቀምም በእኩልነት አገልግሎቱን ተደራሽ ያደርጋል። የዚህን እትም ነጻ ቅጂዎች በአማራጭ ቅርጸት ወይም ቋንቋ ከፈለጉ፣ እባክዎ የDCYF ህዝባዊ ግንኙነቶችን በ 1-800-723-4831 ያግኙ ወይም በኢሜይል **Communications@dcyf.wa.gov** ያግኙ።*

DCYF PUBLICATION FS_0089_AM (11-2024) Amheric